# መልካም ያልሆነ ጕዳና ሠላማዊ ሰፈር አያደርስም!

ሲቲና ከሐረር

ከአንድ ወር በፊት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት “መድረክ” በሚል ሥያሜ የስምንት ፓርቲዎች ጥምረት ነኝ ብሎ ምስረታውን ያበሠረን ስብስብ የምርጫ ስነምግባር ደንብ ድርድሩ ሲካሄድ በቆየባቸው ባለፉት ሁለት ወራት ውስጥ በየሣምንቱ የሚያሠማንን መጨበጫ የሌለውና እርስ በርሡ የሚጠላለፍ አቋም ማራገቡን እንደቀጠለ ነው፡፡ ባለፈው ሣምንት የሥነምግባር ደንቡን ተደራድረድረው ያፀደቁት አራት ፓርቲዎች (ኢህአዴግ፣ መኢአድ፣ ኢዴፓና ቅንጅት) ለሁሉም የአገሪቱ የፖለቲካ ፓርቲዎች በደንቡ ላይ ተወያይተው የሚጨምሩትን ጨምረው፣ የሚቀንሱትን ቀንሰውና የሚሻሽሉትን አሻሽለው እንዲያዳብሩት በምርጫ ቦርድ አማካኝነት የጠሩትን ውይይት “መድረክ” እንደልማዱ ረግጦ ወጥቷል፡፡ ለዚህ እርምጃውም በፊት ሲነገረን የነበረውን ምክንያት (እኛ ከገዥው ፓርቲ ጋር ብቻ ነው መነጋገር የምንፈልገው የሚለውን) ትቶ አዲስ ምክንያት ይዞ ቀርቧል፡፡ የአሁኑ ከ65 በላይ ፓርቲዎች የተገኙበት ውይይት፣ ቀደም ሲል በራሡ ፍቃድ ጥሎት የወጣው የሥነ ምግባር ደንብ ድርድር ቀጣይ ሂደት ያልሆነ ይመስል፣ አዲስና የተለየ ምክንያት ነው የነገረን፡፡ ይህም በምርጫ ሕግ መሠረት ፣ የምርጫ ስነምግባር ደንቡን ማውጣት የምርጫ ቦርድ ሥልጣን ነው፣ ምርጫ ቦርድ በሕግ የተሠጠውን ሥልጣን በአራቱ ፓርቲዎች ተነጥቋል፣ በመሆኑም ውይይቱ ላይ የምሣተፈው ደንቡን ምርጫ ቦርድ በባለቤትነት ከያዘው ነው፡፡ ›› የሚል ነው፡፡

“መድረክ”፣ ከሁለት ወር በፊት የሥነምግባር ደንቡ ረቂቅ ላይ ድርድር ሲደረግ፣ አንዴም ‹‹ ደንቡን የማዘጋጀት ሥልጣን በሕግ የተሠጠው ለምርጫ ቦርድ ነው ›› የሚል ሐሣብ አልተነፈሠም ነበር፡፡ እርግጥ ነው የምርጫ ሕጉ የምርጫ ስነምግባር ደንቡን የማዘጋጀት ሥልጣን የምርጫ ቦርድ እንደሆነ ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ “መድረክ” አጠቃላይ የደንቡን ለማጽደቅ የተደረገውን የድርድር ሒደትና የተደረሠበትን ሥምምነት፣ እንዲሁም የሥነ ምግባር ደንብ የማዘጋጀት መርሖችን

ዘንግቶት ሳይሆን ለፈጠረው ጥልፍልፍ የማምለጫ ሠበብ ይሆነኛል ብሎ ነው የወረወረው፡፡

በቅድሚያ በማንኛውም ተመሣሣይ ሙያ ላይ የተሠማሩ ወይም የጋራ አላማ የሚያስፈፅሙ ግለሰቦች፣ ድርጅቶች - የፖለቲካ ፓርቲዎች ጭምር በጋራ በስምምነት ወይም የሚመሩበት/የሚገዙበት የሥነምግባር ደንብ የማዘጋጀት መብት ያላቸው መሆኑ ይታወቃል፡፡ ለምሣሌ በ97 ምርጫ ኢሕአዴግ አባላቱና እጩዎቹ የሚገዙበትን የራሡን የሥነምግባር ደንብ አዘጋጅቶ ነበር፡፡ በመድረክ ስር የተሠባሠቡት ፓርቲዎች፣ ሌሎቹም የፖለቲካ ፓርቲዎች አባሎቻቸውና እጩዎቻቸው የሚገዙበት የምርጫ ስነምግባር ደንብ የማዘጋጀት መብት አላቸው፡፡ ሁሉም ሕጋዊ እውቅና ያላቸው የአገሪቱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም የተወሰኑት አባሎቻቸውና እጩዎቻቸው የሚገዙበትን የሥነምግባር ደንብ የማዘጋጀት መብት አላቸው፡፡ የሚዘጋጀው ደንብ ሕገወጥ አካሄድን የሚፈቅድ ወይም የሚያበረታታ ካልሆነ፣ ማንም ይህን መብት ሊከለክላቸው አይችልም፡፡

የፖለቲካ ፓርቲዎችን መዝግቦ ሕጋዊ እውቅና የመስጠትና አሠራራቸውን የመከታተል ሥልጣን በሕግ በተሠጠው ምርጫ ቦርድም ሁሉም የአገሪቱ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚገዙበት የምርጫ ስነምግባር ደንብ የሚዘጋጅበት አካሄድም አለ "መድረክ" አራቱ ፓርቲዎች ተደራድረው ባፀደቁት የሥነምግባር ደንብ ላይ ፓርቲዎች እንዲወያዩ የተጠራውን ስብሠባ ረግጦ ሲወጣ፣ ‹‹በምርጫ አዋጁ ደንቡን የማዘጋጀት ሥልጣን የተሠጠው ለምርጫ ቦርድ እንጂ ለፖለቲካ ፓርቲዎች አይደለም፣ ሕግ ተጥሷል - ምርጫ ቦርድ ስልጣኑን ተነጥቋል›› የሚል ጩኸት ማሰማቱ ከቅንነት በመነጨ የመቆርቆር ስሜት ሳይሆን በተደጋጋሚ የሠሩትን ስህተት ለመደበቅ የፈጠሩት ተራ ምክንያት ነው፡፡

ሌላው "መድረኩ" የዘነጋው ጉዳይ፣ አራቱ ፓርቲዎች ተደራድረው ደንቡን ሲያፀድቁ፣ ደንቡ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ የአገሪቱ የምርጫ ሕግ አካል ሆኖ እንዲፀድቅ መስማማታቸውን ነው፡፡ እነዚህ አራት ፓርቲዎች ለሁሉም የአገሪቱ የፖለቲካ ፓርቲዎች የውይይት ጥሪ ያቀቡት ደንቡ ሕግ ሆኖ እንዲፀድቅ

ለተወካዮች ም/ቤት ከመቅረቡ በፊት፣ ይዘቱ ላይ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ሳይሆን የሚዳብርበትንም ሁኔታ ለማመቻቸት ነው፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ “መድረክ” የረገጠው ሌላው ጉዳይ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አሠራርና የአባላት ሥነምግባር ደንብ መሠረት፣ የፓርላማ ቡድኖች፣ በም/ቤቱ መቀመጫ ያላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎችና፣ የም/ቤቱ አባል የሆኑ ግለሠቦች ሕግ የማመንጨት መብት ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ በዚህ መሠረት አራቱ ፓርቲዎች ተስማምተው ያፀደቁትን የምርጫ ስነምግባር ደንብ፣ የተቀሩትን ፓርቲዎችን ማያወያዩ፣ በተስማሙት መሠረት ሕግ ሆኖ እንዲፀድቅ ለምክር ቤቱ ማቅረብ ይችሉ ነበር፤ ነገር ግን የተቀሩት የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዲወያዩበት ማድረጋቸው፣ ደንቡን ያፀደቁት አራት ፓርቲዎች ያላዩትና በደንቡ ውስጥ መካተት ያለባቸውም ሐሣብ ካላቸው በደንቡ ውሰጥ ተካተው የሚዳብርበትን ሁኔታ ከመፍጠር፣ ከሕግም ከሞራልም አኳያ ተገቢና ቀና ከሆነ አመለካከት የመነጨ ነው፡፡ የደንቡ ሕግ ሆኖ መጽደቅ አለመጽደቁ፣ በም/ቤቱ አብላጫ ድምፅ የሚወሰን ነው፡፡ ይህን ደንብ የተወካዮች ምክር ቤት ሕጉን መርምሮ ሊያፀድቀውና የሀገሪቱ የምርጫ ሥነ ምግባር ደንብ ሊያደርገው ይችላል፡፡

በአራቱ ፓርቲዎች የፀደቀውና የተቀሩት ፓርቲዎች ተወያይተውበት ሕግ ሆኖ እንዲፀድቅ ለተወካዮች ም/ቤት ሊቀርብ በተዘጋጀው የምርጫ ሥነምግባር ደንብ ዙሪያ ያለው እውነታ ከላይ የተገለፀው ነው፡፡ ይህ ሆኖ ሣለ መድረክ ‹‹ ፓርቲዎቹ ደንቡን የማውጣት ስልጣን የላቸውም ፣ ሕጋዊ ስልጣን ያለው ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ነው፣ ቦርዱ ስልጣኑን ተቀምቷል፡፡ የደንቡ ባለቤት ቦርዱ ካልሆነ በውይይቱ ላይ አልሣተፍም፣ ምንትስ ምንትስ›› ያስባለውን ምክንያት “መድረክ” እንደ ተቋም ካሉት ውስጣዊ ችግሮችና ከአመራሮቹ የእስከዛሬ አካሄድ በመነሣት መገመት ይቻላል፡፡

ሰሞኑን የመድረክ አመራሮች የሰጡትን መግለጫም መጥቀስ ይቻላል፡፡ አንድ የመድረክ አመራር ነኝ የሚል ግለሰብ በኢቲቪ የተናገረው ቃል እጅግ በጣም

የሚገርም ነው፡፡ "ይህ ተስማማንበት የሚሉት ሰነድ 'IDEA' ከሚባል ድርጅት እንዳለ የተገለበጠ ነው፡፡ ይህንን የተገለበጠ ሰነድ አራቱ ፓርቲዎች ሌክቸረር፣ እኛ ደግሞ ተማሪ እንድንሆን አንፈልግም" በሚል ከድርድሩ አቋርጠው መውጣታቸውን በይፋ ሲናገሩ ተሰምተዋል፡፡ እኛ እንደተከታተልነውና እንደተረዳነው ከ65 በላይ የሚሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች በጋራ በመወያየት ስምምነት ላይ ለመድረስ ያደረጉት እንጂ አንዱ አስተማሪ ሌላው ተማሪ የመሰለበት እኔ አውቅ እኔ አውቅ አካሄድ የታየበት አልነበረም፡፡

ከመድረክ ከፍተኛ አመራሮች መካከል፣ የወቅቱን ሊቀመንበሩን ዶ/ር መራራ ጉዲና ጨምሮ ገሚሆቹ የረጅም ጊዜ የፖለቲካ ተሞክሮ እንዳላቸው ይታወቃል፡፡ የአሁኑን አቋም ሲይዙ ፣ የምርጫ ሕግ እንዲሁም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አሠራርና የአባላት ሥነምግባር ደንብ በፀደቁበት ጊዚያት ጭምር የምክር ቤቱ አባል የነበሩም አሉ፡፡ በመሆኑም የምርጫ ስነ ምግባር ደንብ የሚዘጋጅበትን መርሕና ለምክር ቤት የሚቀርብ ሕግ የሚመነጭበትን ሕጋዊ አካሄድ አያውቁት ይሆናል ብሎ ማሠብ አጉል የዋህነት ነው፡፡ ከዚህ ይልቅ የያዙት አቋም ከውስጥ ችግራቸው የመነጨ፣ መሆኑን ምናልባትም ከጀርባው ስውር አላማ መኖሩን ነው የሚያመላክተው፡፡

በመድረክ ውስጥ ያለውን ሁኔታ ስንመለከት፣ በራሡና በሥሩ ያሠባሠባቸው ፓርቲዎች ውስጥ ችግሮች መኖራቸውን መገንዘብ አያዳግትም፡፡ እንደሚታወቀው ስምንቱ ፓርቲዎች በመድረክ ሥር የተሠባሠቡት ተመሣሣይ የጋራ አላማ ኖሯቸው አይደለም፡፡ ፓርቲዎቹ የተለያዩ ብሔሮችና ብሔረሠቦች አመለካከቶችን ስለሚወክሉ በአንድ ሥያሜና የምርጫ ምልክት ለምርጫ ቀርበው በርካታ የምክር ቤት መቀመጫ ሥልጣን የማግኘት ሕልም ነው ያሰባሰባቸው፡፡ ይህ ከአላማ ይልቅ በግል ጥቅም ላይ የተመሠረተ ስብስብ፣ መሆኑ በአመራሮቹ መሐከል አለመተማመንን ፈጥሯል፡፡ የስብስቡ ምክር ቤት እንደ አንድ አካል በአንድ ጉዳይ ላይ በአብላጫ ድምፅ ውሣኔ ከማሣለፍ ይልቅ በስምምነት መወሠንን የመረጠውም፣ ውሣኔዎች በድምፅ ብልጫ መተላለፋቸው አንዱ በሌላው ላይ አላማውን የሚጭንበትን መንገድ ይከፍታል ከሚል ያለመተማመን ከፈጠረው ሥጋት የመነጨ ነው፡፡ የፓርቲዎቹ አላማ የተለያየ ብቻ ሣይሆን፣ እርስ በርስ የሚቃረን በመሆኑ፣

ያለመተማመናቸው ካስከተለው ውሣኔዎችን በድምፅ ብልጫ ማሣለፍ ካለመቻላቸው ጋር ተዳምሮ፣ በአንድ ጉዳይ ላይ በሚፈለገው ጊዜ ውስጥ የጋራ አቋም መያዝ ተስኗቸው ጊዜያቸውን በንትርክ ለማባከን ዳርጓቸዋል፡፡ በእነዚህ ምክንያቶች ተወያይቶ ከመግባባት መድረስ እንደሠማይ ርቋቸው፣ አቋም መያዝ የሚያስፈልገው ጉዳይ ሲገጥማቸው፣ መርምረው ያልተገነዘቡትንና ፊት ለፊት ያገኙትን ሐሣብ በዘፈቀደ ከማቅረብ ውጭ አማራጭ አጥተዋል፡፡ የባለፈው ሣምንት የፓርቲዎች ውይይት ላይ ድርድሩ ሲካሄድ ያላነሡትን፣ ጭራሽ ገለልተኛ አይደለም ሲሉት የቆዩትን ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ስልጣኑ ተቀምቷል፣ አካሄዱ ሕገወጥ ነው ስለዚህ በውይይቱ ላይ አንሣተፍም የሚል መሠረተ ቢስ አቋም መነሻም ይሔው ነው፡፡ መድረኮች ያቀረቡት ተራ ምክንያት ለህብረተሰቡ ያላቸው ንቀት አመላካች ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች ለምርጫ ቦርድ መብት ተከራካሪ የሆኑት ከመቼ ወዲህ ነው፡፡

የመድረክ ፓርቲዎች አላማና አመለካከት የአንዱ ከሌላው የተለየና የሚቃረን በመሆኑ አላማችን በጥምረቱ  ተውጧል የሚል ሌላ ሥጋትም ፈጥሮባቸዋል፡፡ እያንዳንዳቸው ቀደም ሲል የነበረንን ደጋፊ አጥተናል ወይም እናጣለን የሚል ሥጋት አሣድሮባቸዋል፡፡ ይህ ሥጋት በመጪው ምርጫ ላይ የመሣተፍ፣ ያለመሳተፍ ኹዋኹዌ ውስጥ ከቷቸዋል፡፡ የማይሣተፉ ከሆነ ደግሞ ምክንያቱን ለሕዝብ መግለጽ ይኖርባቸዋል፡፡ ምክንያቱ የውስጥ ችግራቸው መሆኑን ማሣወቅ የሚያስከትለውን ዘላቂ አደጋ ስለሚያሣያቸው፣ ሌሎች ሠበቦች ያስፈልጓቸዋል፡፡ መንግስት፣ ገዥው ፓርቲ፣ እና ሌሎች ጠላቶቻችን ናቸው ያሉዋቸው ፓርቲዎች፣ የፖለቲካ ምህዳሩን አጥብበው መላወሻ አሣጡን ማለትና ( ባለው የፓለቲካ ምህዳር መጠቀም አለመፈለጋቸው ሣይዘነጋ ) ለዚህ ማሣመኛ ሠበብ መፍጠር ነው፡፡ በተለይ የምርጫ ስነምግባር ደንብ ድርድር ላይ፣ በተደራዳሪዎች ከፀደቀም በኋላ የተጠራው የፓርቲዎች ውይይት ላላለመሣተፍ ያቀረቡዋቸው የማይጨበጡ ሠበቦች ይህን አካሄዳቸውን አጋልጧል፡፡

የመድረኩ ፓርቲዎች ፍፁም የተራራቀና ተቃራኒ አቋም ይዘው መጣመራቸው፣ ሕዝብ፣ አቋምና ፖሊሲያቸው ምን እንደሆነ ማየት ተስኖት ፊቱን የሚያዞርባቸው መሆኑን ተረድተዋል፡፡ ይህም የህዝብን ይሁንታ ለማግኘት በመሠረተ ቢስ ወሬ

የመንግስትንና የገዥውን ፓርቲ በጎ ገጽታ በማቆሸሽ ከሕዝብ ጋር አራርቀውት ሠላማዊ ያልሆነ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ለመለኮስ ሁኔታዎችን እንዲያመቻቹ አስገድዷቸዋል፡፡ አሁን ያለው የአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ ግን ሠላማዊ ያልሆነ የፖለቲካ እንቅስቃሴን የሚፈቅድ አይደለም፡፡ ምርጫ 97ን ተከትሎ የተቀሠቀሠው ሁከት ፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንደሸንበቆ ተመዞ የወጣው ቅንጅት ‹‹አለ›› ሲባል በውስጥ ችግሩ ተፈረካክሶ አመራሮቹ ጎራ ለይተው በጠላትነት በመተያየት አገሪቱን ወደ ብጥብጥ እንዲታመራ አድርገው ነበር፡፡ አሁንም  “መድረክ” በሚል ስያሜ የተሰባሰቡት የፖለቲካ ፓርቲዎች በአላማ አንድነት ሳይሆን እንዲሁ በዘፈቀደ ገዥውን ፓርቲ እንቃወማለን የሚሉ እንደሆነ ሕዝቡ ተገንዝቧል፡፡ እንዲህ አይነቱ ስብስብ ደግሞ የት እንደሚያደርስ ከዚህ ቀደም ልምዳችን ልንረዳ ይገባል፡፡ ከባለፈው የተማሩት የቅንጅት አካል የነበሩና ከገዥው ፓርቲ ጋር የማይታረቁ ጽንፈኞች ይመስሉ ከነበሩት አንዳንድ ፓርቲዎች ሠላማዊ የፖለቲካ መንገድን ለመከተል መወሠናቸው፣ ሕዝብ አማራጭ ፓርቲዎችን የማግኘት ተስፋ ፈጥሮለታል፡፡ በአገራችንም የድርድር ፖለቲካ እንዲዳብር የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እያበረከቱ መሆናቸው ሊመሰገን የሚገባ ነው፡፡

እነዚህ ፖለቲካዊ ነባራዊ ሁኔታዎች ናቸው ሠላማዊ ያልሆነ ትግልን ማካሄድ የማይቻል የሚያደርጉት፡፡ “መድረክ” ሠላማዊ አካሄድን ተከትሎ የሕዝብ ድጋፍ የማግኘት አማራጭ እያለ፣ የሚከተለው መንገድ የሚያዛልቅ ይሁን አይሁን መመርመር ተስኖት በተገኘው መንገድ ስልጣን ላይ ለመውጣት የሚጋለበው የስሜት ፈረስ ገደል ከቶት ታሪክ ሆኖ እንዲቀር ከማድረግ ያለፈ የትም እንደማያደርሠው አመራሮቹ ሊገነዘቡ ይገባል፡፡ ሕዝብም የመድረኩን አካሄድ በጥንቃቄ ሊያስተውለው ይገባል እላለሁ፡፡ የፖለቲካ ትግል፤ አካሄዱም መድረሻውም ሠላማዊና ዴሞክራሲያዊ መሆን አለበት፡፡ መልካም ያልሆነ ጎዳና፣ ሠላማዊ ሥፍራ ሊያደርስ አይችልምና፡፡